# የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን

# የቴሌኮሙኒኬሽን መሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን መመሪያ

## ለባለድርሻ አካላት ምክክር የቀረበ ረቂቅ

ነሀሴ 2012

# የቴሌኮሙኒኬሽን መሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን መመሪያ

የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 ("አዋጁ") አንቀጽ 6 (2) በኢትዮጵያ ውስጥ የኮሙኒኬሽን ፖሊሲዎችን የማስፈጸም ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 44 (5) መደበኛ የቴክኒክ ደረጃን እና የንግድ ሁኔታዎችን ጨምሮ የኮሎኬሽን ቦታን በተመለከተ መመሪያ የማውጣት ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 44 (10) የቴክኒክ ደረጃን እና የንግድ ሁኔታዎችን ጨምሮ የመሠረተልማት መጋራት መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 54 (2) መሠረት አዋጁን እና አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦችን የማስፈጸሚያ መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ይህንን የቴሌኮሙኒኬሽን መሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## አጭር ርዕስ፣ ትርጓሜ፣ ዓላማ፣ የተፈጻሚነት ወሰን

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የቴሌኮሙኒኬሽን መሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን መመሪያ ቁጥር 7/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜዎች</u>

በዚህ መመሪያ በጥቅም ላይ የዋሉ ቃላቶችና ሐረጎች በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 የተሰጣቸው ትርጉም እና አፈጻጸም ይኖራቸዋል። የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1) **"የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ"** ማለት የኮሎኬሽን ቦታ ወይም መሠረተ ልማት የመጋራት አገልግሎቶችን ለሌሎች የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የሚያቀርብ ነው፤

2) **"የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ፈላጊ"** ማለት ከመሠረተልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን አገልግሎት አቅራቢ የኮሎኬሽን ቦታ ለማግኘት ወይም መሠረተ ልማት ለመጋራት የሚፈልግ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ነው፤

3) **"መሠረተልማት የማጋራት እና የኮሎኬሽን አገልግሎቶች"** ማለት ለኮሎኬሽን ዓላማዎች ወይም የመሠረተ ልማት መጋራት በአንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለሌላኛው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚቀርብ አገልግሎት ነው፤

4) **"ገባሪ መሠረተ ልማት"** ማለት አንቴናዎችን፣ ሰዋቾችን፣ ሰርቨሮችን፣ የመረጃ ቋቶችን፣ የማከፋፈያ ወይም የሬዲዮ መዳረሻ ኖድ እና የማስተላለፊያ መሣሪያዎችን ጨምሮ በገባሪ የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ንብርብር ላይ ያሉ ክፍሎች ወይም አካላት ናቸው፤

5) **“ባለሥልጣን”** ማለት በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ነው፤

6) **“ኮሎኬሽን”** ማለት አንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለአገልግሎት አቅርቦት የሚጠቀምባቸውን የኔትወርክ መሣሪያዎች ወይም ሥርዐቶች የተገጠሙበት ስፍራ ላይ በሁለቱ መካከል በሚደረሰው ስምምነት መሰረት ቴክኒካዊ አግባብነት ባለው ቦታ በአንድ ላይ ማስቀመጥ ነው፤

7) **“የመሠረተ ልማት መጋራት”** ማለት በተዋዋዮቹ መካከል የሚደረገው ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኔትወርክ ክፍሎችን፣ ሥርዓቶችን፣ መሣሪያዎችን፣ አገልግሎቶችን፣ ቅጥር ግቢዎችን የመጠቀም መብቶችን ጨምሮ በእነዚህም ሳይወሰን የመሠረተልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን አገልግሎት አቅራቢ ከመሠረተ ልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን ጠያቂ ጋር ቋሚ እና ገባሪ መሠረተ ልማቶችን የሚጋሩበት ሂደት ነው፤

8) **“የማገናኘት አገልግሎቶች”** ማለት የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ግንኙነቶችን ለማሳካት በአንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለሌላው የሚሰጡ አገልግሎቶች ናቸው፤

9) **“ቋሚ መሠረተ ልማት”** ማለት የሥራ ቦታዎችን፣ ሕንፃዎችን፣መጠለያዎችን፣ማማዎችን፣ ረዣዥም ቋሚዎችን፣ ምሶሶዎችን፣መለስተኛ ጉድጓዶችን፣ጠባብ ቦዮችን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እና የአየር ማቀዝቀዣን ጨምሮና በእነዚህም ሳይወሰን የገባሪ ቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ መሠረተ ልማት ንብርብር አካል ያልሆነ መሠረተልማት ነው፤

10) **“ተጠያቂ ኦፕሬተር”** ማለት ከሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የመሠረተልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን አገልግሎቶች ጥያቄን የተቀበለ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ነው፤

11) **“ጠያቂ ኦፕሬተር”** ማለት ከሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የመሠረተልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን አገልግሎቶችን የሚጠይቅ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ነው፤

12) **“የቴሌኮሙኒኬሽን ችርቻሮ አገልግሎት”** ማለት ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ሳይሆን ለህዝብ በቀጥታ የሚቀርብ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ነው።

## 3. <u>ዓላማዎች</u>

የዚህ መመሪያ ዋነኛ ዓላማዎች-

1) የመሠረተ ልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን ስምምነቶችን የሚገዛ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፤

2) በአዋጁ አንቀጽ 44 መሠረት የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽንን ለመቆጣጠር ባለሥልጣኑ ሊከተል የሚገባቸውን ደንቦች እና አሠራርሮች ግልፅ እንዲሆኑ ማድረግ፤

3) የኔትወርክ ዝርጋታ ወጪን መቀነስ፤

4) የሀገሪቱ የመልክዓ ምድር ገፅታ እንዳይለወጥ የማማዎች ተከላና መስፋፋትንም በመቀነስ አካባቢን መጠበቅ፤

5) የመግቢያ እና የማስፋፍያ ተግዳሮቶችን በመቀነስ በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል ውድድርን ማዳበር፤

6) የኔትወርክ አቅምና ብቃት ፣ የማሰራጫና የመቀበያ ጣቢያዎችን፣ ዋና መስመሮችን ፣ ማማዎች እና የኔትወርክ አገልግሎቶች ኢንቬስትመንት መደራረብ መቀነስን ጨምሮ እና በእነዚህም ሳይወሰን የኔትወርክ መሠረተልማት አጠቃቀምን ማሳደግ፤

7) መሠረተ ልማትን ከመጋራት የሚገኙትን ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ለአጠቃላዩ የቴሌኮሙኒኬሽን ባለድርሻ አካላት ጠቀሜታ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፤

8) በደንበኞች ላይ የሚጣል የክፍያ ተመን የመቀነስ ተጨማሪ ውጤት ያለው ወጪን በመቀነስ ብቃትን የማሳደግ ፖሊሲ እንዲከተሉ ማበረታታት፤ እና

9) በመሠረተልማት ግንባታ እና/ወይም ዝርጋታ ከሚሳተፉ ሌሎች የመንግሥት ተቋማት ጋር ባለሥልጣኑ እንዲቀናጅና እንዲተባበር ማስቻል፤

ናቸው፡፡

4. <u>የተፈጠዓሚነት ወሰን</u>

ይህመመሪያ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪብሊክ በሚገኙ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የባለሥልጣኑ ሚና

5. <u>የባለስልጣኑ ሚና</u>

1) ባለሥልጣኑ

(ሀ ) በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን.አገልግሎቶች አቅርቦት ለማመቻቸት ጥረት የደርጋል፤

(ለ) የመሠረተልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን አገልግሎቶችን ይቆጣጠራል፤

ሐ) በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል የመሠረተልማት መጋራትእና የኮሎኬሽን አገልግሎቶች አቅርቦቶች የሚመሩባቸው ደንቦች በከፍተኛ ደረጃ ተአማኒነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤

(መ) ተዋዋይ ወገኖች በመሠረተልማት መጋራትእና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች ድርድር ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ በአዋጁ አንቀጽ 44 (4) እና 44 (9) መሠረት የስምምነቱን የውል ቃሎች ለመወሰን ጣልቃ ይገባል፤ እና

(ሠ) አግባብ ባላቸው ፈቃድ (ዶች) መካከል ወጥነት እንዲኖር ለማድረግ እና በዚህ መመሪያ ወይም በባለሥልጣኑ ከወጡ ሌሎች መመሪያዎች ጋር መጣጣሙን ለማረጋገጥ በማናቸውም ጊዜያት የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነቶችንን የመመርመር መብት አለው፡፡

2) ባለሥልጣኑ፤

(ሀ) በራሱ ሥልጣን ወይም በመሠረተልማት መጋራት እና በኮሎኬሽን ስምምነት ተዋዋይ ወገን ጥያቄ በአዋጁ አንቀጽ 45 ወይም በባለሥልጣኑ በፀደቀ ማናቸውም መመሪያ መሠረት የመሠረተልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን ክፍያዎች ሕጋዊ መሆን አለመሆናቸውን ለመወሰን ጣልቃ ይገባል፤

(ለ) በራሱ ሥልጣን ወይም በመሠረተልማት መጋራትእና ኮሎኬሽን ስምምነት ተዋዋይ ወገን ጥያቄ በመሠረተልማትመጋራትእና ኮሎኬሽን ስምምነት ላይ የሚነሳ አለመግባባትን በዚህ መመሪያ እና በባለስልጣኑ አለመግባባትን ለመፍታት በወጣው መመሪያ ውስጥ በተጠቀሱት ዘዴዎች መሠረት መፍታት ይችላል፤

(ሐ) ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች አቅርቦት ሲባል የሚከናወን የመሰረተ ልማት ዕቅድን፣ ግንባታን እና መጋራትን ለማሳለጥ ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር መቀናጀት ይችላል፤ እና

(መ) ለመጋራት የሚችሉትን የመሠረተልማቶችን ዝርዝር ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊወስን ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት
## አጠቃላይ መርሆዎች

### 6. <u>አጠቃላይ የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን መርሆዎች</u>

ሁሉም የመሠረተልማት መጋራትእና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች ስምምነቶች ከግልፅነት፣ከአድልዎ አለመኖር እና ከሕጋዊ ታሪፎች መርሆዎች ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው፡፡

1) ግልፅነት:

(ሀ) ከመሠረተልማት መጋራትእና ኮሎኬሽን አገልግሎት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ውሳኔዎችን በሚመለከት ባለሥልጣኑውሳኔ ለመስጠት የሚያልፍባቸው ሂደቶች የሚታዩ እና ግልፅ መሆን አለባቸው፡፡

(ለ) በመሠረተልማት ማጋሪያ እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች አቅርቦት በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ገበያዎች ለመሠረተልማት መጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን አገልግሎት ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው በባለሥልጣኑ የተወሰነለት የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር በባለሥልጣኑ የፀደቀውን የመሠረተ ልማት መጋራት አቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ እንዲታተም ማድረግ ይኖርበታል፡፡

(ሐ) ባለሥልጣኑ የፀደቀውን የመሠረተ ልማት መጋራት አቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ በድረ ገፁ ላይ ያወጣል፤ተጠያቂው ኦፕሬተር ይህንኑ ለጠያቂው ኦፕሬተር ያለክፍያ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2) አድልዎ አለማድረግ;

አድልዎ ያለማድረግ መርህ የመሠረተልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን አገልግሎቶች አቅርቦት የውል ቃሎችና ሁኔታዎች የመሠረተልማትመጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች አቅራቢ እነዚሁኑ የመሠረተልማትመጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች ለራሱ ከሚያቀርብበት ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ያስገድዳል፡፡

3) ሕጋዊ ክፍያዎች

ክፍያዎች ግልፅ፣አድልዎ የሌለባቸው፣አሳማኝ እና ምክንያታዊ መሆን አለባቸው፡፡ ለመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች የሚከፈለው ክፍያ በአዋጁ አንቀጽ 45 እና በባለስልጣኑ በተደነገገ ማንኛውም መመሪያ መሠረት ሕጋዊ መሆን አለበት፡፡

## ክፍል አራት
## ኮሎኬሽን እና የመሠረተልማት መጋራት ሥርዐቶች

### 7. መብቶች እና ግዴታዎች

1) ሁሉም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች የመሠረተልማት መጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን አገልግሎቶችን ከማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር የመጠየቅ መብት አላቸው፤ተጠያቂውና ጠያቂው ኦፐሬተሮች በተጠቀሱት አገልግሎቶች የስምምነት የውል ቃሎች ላይ በቅን ልቦና መደራደር አለባቸው፡፡

2) መሠረተልማትን ለመጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን አገልግሎቶች አግባብ ባለው ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው በባለሥልጣኑ የተወሰነለት ተጠያቂ ኦፐሬተር ለአገልግሎቶቹ ከጠያቂው ኦፐሬተር ጋር ስምምነት ላይ ለመድረስ በቅን ለቦና የመደራደር ግዴታ አለበት፡፡

3) ተጠያቂው ኦፐሬተር በሚከተሉት ምክንያቶች ቴክኒካዊ አግባብነት ከሌለው ብቻ የተጠየቀውን የመሠረተልማት መጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን አገልግሎት ውድቅ የማድረግ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

   (ሀ) ያለመጣጣም ጉዳዮች፤ ወይም

   (ለ) ለቴሌኮሙኒኬሽን ኔትዎርክና አገልግሎት ደህንነት፣ አስተማማኝነት እና ታማኝነት ከፍተኛ አደጋ ካለው፡፡

### 8. በቅን ልቦና የሚደረግ ድርድር

1) በመሠረተልማት መጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን አገልግሎቶች ስምምነት ላይ በሚሳተፉ ኦፐሬተሮች መካከል የሚደረግ ድርድር በቅን ልቦና መካሄድ አለበት፡፡ ከመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች ጋር የተያዙ አለመግባባቶች የተከሰቱ እንደሆነ አለመግባባቶችን በሙሉ ለመፍታት ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡

2) በቅን ልቦና በሚደረጉ ድርድሮች እያንዳንዱ ተደራዳሪ የሚከተሉትን ማድረግ የለበትም:፤-

   (ሀ) ሌላኛውን ወገን ሆን ብሎ ማሳሳት፤

   (ለ) ሌላኛውን ወገን  በኃይል ወይም በመጫን ስምምነት ላይ እንዲደርስ ማስገደድ፤እና፣

   (ሐ) ሆን ብሎ ድርድርን ማደናቀፍ፤

3) የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም በቅን ልቦና የመደራደር መርሆዎችን እንደመጣስ ያስቆጥራል፤

   (ሀ) ለሌላው ኦፐሬተር ተገቢ መረጃዎችን ሁሉ በወቅቱ አለመስጠት፤

   (ለ) ጫና የሚያሳድሩ ወይም ያለአግባብ የተለጠጡ ወይም ገደብ የሚጥሉ ሚስጥርን ያለመግለጽ ስምምነቶችን እንዲፈረም መጠየቅ፤

   (ሐ) ለወደፊት ማሻሻያዎችን ለማድረግ የሚፈቅድ ድንጋጌ በስምምነት ውስጥ እንዲካተት አለመፍቀድ፤

   (መ) በስምምነቱ ውስጥ የተካተቱትን የውል ቃሎች እና ሁኔታዎችን ከጉዳዩ ጋር የማይዛመዱ ጉዳዮችን እልባት ከመስጠት ጋር ለማያያዝ መሞከር፤

(ሠ) ገዥ ውሳኔዎችን ለመፈጸም ሥልጣን ያለውን ሰው ለመሰየም በተደጋጋሚ ፈቃደኛ አለመሆንን ጨምሮ እና በዚህም ሳይወሰን ድርድርን የማዘግየት ድርጊቶችን መፈጸም፤ እና

(ረ) በባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚወስነው መሠረት በቅን ልቦና የመደራደርን መርህ ይጥሳሉ ብሎ ሊቆጥራቸው የሚችላቸውን ሌሎች ደርጊቶች መፈጸም፡፡

9. <u>*የመሠረተልማት መጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን አገልግሎቶችን መጠየቅ*</u>

1) አንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር የመሠረተልማት መጋራት እና/ወይም የኮሎኬሽን አገልግሎቶችን ጥያቄ ለሌላ ኦፐሬተር ሲያቀርብ ጠያቂው ኦፐሬተር ጥያቄውን እንደሚከተለው ያቀርባል፤

(ሀ) በጽሑፍ ለተጠያቂው ኦፐሬተር ማቅረብ፣

(ለ) ድርድሩን ለመጀመር የታሰበበትን ቀን፣ የመሠረተልማት መጋራት እና/ወይም የኮሎኬሽን አገልግሎቶችን የሚፈለግበትን ቀን እና የቴክኒክ መስፈርቶችን ጨምሮ እና በእነዚህም ሳይወሰን ከተጠየቀው መሠረተልማት መጋራት  እና ኮሎኬሽን አገልግሎት ዓይነት ጋር የተያያዙ የተሟሉ መረጃዎችን ማካተት፤ እና

(ሐ) ስለ አቀረበው ጥያቄ በአምስት (5) የሥራቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ፡፡

2) ተጠያቂው ኦፐሬተር፤

(ሀ) ከመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጋር የተያያዙ ደርድሮችን በታቀደው ቀን መጀመር፤

(ለ) የተየቀውን የመሠረተልማት ማጋሪያ እና ኮሎኬሽን አገልግሎት ቅፅ ማቅረብ፤እና

(ሐ) የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎትን በጠያቂው ኦፐሬተር በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማቅረብከቻለ ተጠያቂው ኦፐሬተር ለጠያቂው ኦፐሬተር ጥያቄውን በተቀበለ በአሥራአምስት (15) የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

3) ተጠያቂው ኦፐሬተር የተጠየቀውን የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎት መስጠት የሚችል መሆኑን ለጠያቂው በማሳወቅ የፀደቀ የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ ካለ ቅጂውን ይሰጣል፤ እንዲሁም የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎት ጥያቄ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ አስራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ድርድሩን መጀመር ይኖርበታል፡፡

4) ተጠያቂው ኦፐሬተር እና ጠያቂው ኦፐሬተር በቅን ልቦና መደራደርና ድርድሩን ለማጠናቀቅ የሚቻላቸውን ሁሉ ጥረት በማድረግ ድርድሩ በተጀመረ ሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወይም ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በተስማሙበት ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የመሠረተልማትመጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነት መፈራረም ይኖርባቸዋል፡፡

5) ተጠያቂው ኦፐሬተር እና ጠያቂው ኦፐሬተር የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነት ለመተግበር የሚያስችሉ ዝግጅቶች እና ሁኔታዎች የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነት በተፈረመ ሠላሳ (60) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወይም ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በተስማሙበት ምንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መጠናቀቃቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

6) የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች ጥያቄ ወድቅ የሚሆነው በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 7 (3) በተዘረዘሩት ምክንያቶች ብቻ ሲሆን ተጠያቂው ኦፐሬተር የምክንያቱን አሳማኝነት የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች ጥያቄን በተቀበለ በአሥራ አምስት (15) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በጽሑፍ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

7) ተጠያቂው ኦፐሬተር የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች ጥያቄ ውድቅ የተደረገበትን ኮፒ ወይም ቅጂ እና ውድቅ የተደረገበትን ውሳኔ ለጠያቂው ኦፕሬተር በደረሰው ሰባት (7) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በባለሥልጣኑ ፋይል ውስጥ እንዲያያዝ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

8) በአዋጁ አንቀጽ 44 (4) እና 44(9) መሠረት ባለሥልጣኑ ተጠያቂው ኦፐሬተር ለተጠየቀው የመሠረተልማት መጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን አገልግሎቶች አግባብ ባለው ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዲኖረው የወሰነ እንደሆነ እና ተዋዋይ ወገኖቹ ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ስምምነት ላይ  መድረስ ካልቻሉ ከተዋዋዮቹ አንዱ ለባለሥልጣኑ ይግባኝ ማቅረብ ወይም ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ጣልቃ በመግባት በአዋጁ ከአንቀጽ 35 እስከ አንቀጽ 38 ወይም ያለመግባባትን ለመፍታት በወጣው  መመሪያ መሠረት አስገዳጅ ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት
## የመሠረተልማትመጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነቶች

### 10. <u>የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነቶች</u>

1) ሁሉም የመሠረተልማት መጋራትእና ኮሎኬሽን ስምምነቶች በጽሑፍ ሆነው፤

(ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 የተነገገውን መርሆዎች የተከተሉ፣

(ለ) በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ፊቃዶች የተመለከቱትን የውል ቃሎችን እና ሁኔታዎችን የሚያከብሩ፣

(ሐ) በኢንዱስትሪው በስፋት ተቀባይነት ያገኙ  ወይም በባለሥልጣኑ የፀደቁ ደረጃዎችን የሚያሟሉ፤ እና

(መ) ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ እና  በባለሥልጣኑ ከወጣ ተፈጻሚነት ካለው ማናቸውም መመሪያ ጋር የተጣጣመ፤

መሆን ይኖርበታል፡፡

2) የመሠረተልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን ስምምነት ጠያቂው ኦፕሬተር በህግ መሠረት መፈጸም የሚችለውን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ድንጋጌን  በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገድብ ወይም  እንዳይፈጸም የሚያደርግ መሆን የለበትም፡፡

### 11. <u>የመሠረተልማት መጋራትእና ኮሎኬሽን ስምምነቶችን ፋይል ስለማድረግ</u>

1) የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነት ኮፒን ስምምነቱ በተፈረመ ሰባት (7) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በባለሥልጣኑ ፋይል እንዲያያዝ ማድረግ አለበት፡፡

2) ባለሥልጣኑ ፋይል በተደረገው የመሠረተልማት መጋራትእና ኮሎኬሽን ስምምነት ውስጥ የተካተቱትን የውል ቃሎች እና ሁኔታዎችን መገምገም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በራሱ ሥልጣን ከተዋዋይ ወገኖቹ ከአንዱ ተጨማሪ መረጃዎች መጠየቅ ይችላል፡፡

3) ባለሥልጣኑ የሁለቱን ተዋዋይ ወገኖች ስሱ የንግድ መረጃዎችን ሚስጥራዊነት መጠበቅን ትኩረት በመስጠት ፋይል የተደረገውን የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነት በድኅረ ገጹ ማውጣት የሚችል ሲሆን የመረጃዎቹን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

12. <u>የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነቶች ማሻሻያ</u>

1) ፋይል የተደረገውን የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነት ተዋዋይ የሆኑ ወገኖች በጋራ ስምምነቱን ማሻሻል ወይም ማስተካከል ይችላሉ፡፡ የተሻሻለው ወይም የተስተካከለው ስምምነት በተፈረመ ሰባት (7) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከባለሥልጣኑ ፋይል ጋር መያያዝ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፋይል የተደረገው የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነት ተዋዋይ የሆኑ ወገኖች ስምምነቱን በሚያሻሽሉት የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች ላይ መስማማት ያልቻሉ እንደሆነ ባለሥልጣኑ አለመግባባትን ለመፍታት በወጣው መመሪያ መሠረት የውል ቃሎችን ወይም ሁኔታዎችን ለመወሰን ከተዋዋይ ወገኖቹ በአንዱ ጥያቄ ወይም በራሱ ሥልጣን ጣልቃ መግባት ይችላል፡፡

13. <u>የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነት መቋረጥ</u>

1) የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነት የሚቋረጠው በስምምነቱ የተመለከቱትን የውል ቃሎች በጥብቅ በመከተል ነው፡፡

2) ባለሥልጣኑ ዘንድ ፋይል የተደረገው የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነት ተዋዋይ የሆነ ወገን ስምምነቱን ማቋረጥ ከፈለገ የውሉን ማቋረጫ ምክንያቶች በመጥቀስ ለሌላው ወገን ከስልሣ (60) ቀን ያላነሰ የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት ይኖርበታል፡፡ የተፈጸመ ጥሰት ካለ ማስጠንቀቂያ የሚሰጠው ኦፕሬተር ሌላው ወገን ጥሰቱን እንዲያስተካክል ከሠላሣ (30) የሥራ ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ማስጠንቀቂያ የደረሰው ወገን ጥሰቱን ካላስተካከለ ማስታወቂያ የሰጠው ወገን ስምምነቱን ለማቋረጥ ወይም በባለሥልጣኑ አለመግባባትን ለመፍታት በወጣው መመሪያ መሠረት ባለሥልጣኑ ጣልቃ እንዲገባ መጠየቅ ይችላል፡፡

3) ለቀረበ የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች አግባብ ባለው ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዲኖረው በባለሥልጣኑ የተወሰነ ከሆነ የተቋረጠ የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነት ተዋዋይ ወገን የሆነ የመሠረተልማት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ ባለሥልጣኑ ጣልቃ እንዲገባለት መጠየቅ ይችላል፡፡ በዚህም ጊዜ ባለሥልጣኑ በባለሥልጣኑ አለመግባባትን ለመፍታት በወጣው መመሪያ መሠረት ጣልቃ ሊገባ ይችላል፡፡

4) ለመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች አግባብ ባለው ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዲኖረው የተደረገ የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነትን ያቋረጠ እንደሆነ፣ ስምምነቱ በተቋረጠ በሰባት (7) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ በማስታወቅ የማስጠንቀቂያውን ኮፒ ያስረክባል፡፡

14. <u>የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ</u>

1) የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተደነገጉትን የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምነቶችን አጠቃላይ መርሆዎችን እና የዚህን መመሪያዎች ድንጋጌዎችን መከተል እና የሰነዱ አካል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2) ለመሠረተ ልማት መጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን አገልግሎቶች በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ገበያዎች ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳላቸው በባለሥልጣኑ የተወሰነላቸው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች በሙሉ የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ እንዲፀድቅ በባለሥልጣኑ ዘንድ ፋይል ማድረግ አለባቸው፡፡ የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ ባለሥልጣኑ መመሪያ በሰጠበት ስልሣ (60) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ፋይል መደረግ አለበት፡፡

3) ባለሥልጣኑ የቀረበለትን የመሠረተ ልማት ማጋራት ማጣቀሻ ሰነድን ለመገምገም እና ለህትመት ብቁ መሆኑ አለመሆኑን ለመወሰን ወይም በቀረበው ሰነድ የተካተቱትን የውል ቃሎች ወይም ሁኔታዎች ጣልቃ በመግባት ለማሻሻል ከስልሣ (60) ቀናት የበለጠ ጊዜ መውሰድ የለበትም፡፡ ባለሥልጣኑ እንዲጸድቅ የቀረበውን የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ በስልሣ (60) ቀናት ውስጥ ውድቅ ካላደረገው የቀረበው ሰነድ እንደፀደቀ ይቆጠራል፡፡

4) በባለሥልጣኑ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር፣ የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ የተሻሻለ ሰነድ እስከሚፀድቅ ድረስ ፀንቶ ይቆያል፡፡ የፀደቀ የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ በባለሥልጣኑ ድረ ገጽ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

5) የፀደቀ የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ የያዘ የመሠረተ ልማት መጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን አቅራቢ የተሻሻለውን የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነዱ እንዲፀድቅ በባለሥልጣኑ ዘንድ ፋይል ማድረግ አለበት፡፡

6) ባለሥልጣኑ የተሻሻለውን የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ በመገምገም ለህትመት እንዲበቃ የሚያፀድቀው መሆን አለመሆኑን በሠላሳ (30) ቀናት ውስጥ መወሰን ይኖርበታል፡፡ ባለሥልጣኑ እንዲጸድቅ የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ካላደረገው ወይም ሰነዱን በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ጣልቃ ገብቶ ካላሻሻለው የተሻሻለው የመሠረተ ልማት ማጋራት ማጣቀሻ ሰነድ እንደፀደቀ ይቆጠራል፡፡

7) ባለሥልጣኑ እርሱ ዘንድ ፋይል የተደረገውን ወይም የፀደቀውን የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ፤ የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች፤

(ሀ) የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ ወይም የሰነዱ ማናቸውም ድንጋጌ ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ ወይም በባለሥልጣኑ ከፀደቀ ተፈጻሚነት ካለው ማናቸውም መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ፤

(ለ) ባለሥልጣኑ ጣልቃ መግባቱ ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው፡፡

በራሱ ሥልጣን ወይም ከቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር የቀረበን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ጣልቃ በመግባት ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

8) ባለሥልጣኑ በእርሱ ዘንድ ፋይል የተደረገውን ወይም የፀደቀውን የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ ለማሻሻል ጣልቃ ለመግባት ከወሰነ በአዋጁ አንቀጽ 36 እና አንቀጽ 37 መሠረት እና ከዚህ በታች የተመለከቱትን በመከተል ተገቢ የሆኑትን መሻሻያዎች ግልጽ በሆነ አሠራር መወሰን ይኖርበታል፤

(ሀ) መደበኛ የአሠራር ሂደትን በመከተል የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድን ለማሻሻል መዘጋጀቱን ለሕዝብ ማስታወቂያ በማውጣት በጉዳዩ ያገባኛል ለሚሉ ወገኖች ያሳውቃል፡፡ ማስታወቂያውም የትኛው ድንጋጌ እንደሚሻሻልና ለምን እንደሚሻሻል የሚያሳይ ግልጽ የሆነ መግለጫ የያዘ ሆኖ ሰነዱ፤

(1) በአዋጁ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን መሆኑን፤

(2) ከዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን መሆኑን፤ ወይም

(3) በባለሥልጣኑ በፀደቁ ተፈጻሚነት ባለው መመሪያ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን መሆኑን፤

(4) የሕዝብን ጥቅም የማያስጠብቅ መሆኑን፤

ማሳየት ይኖርበታል፡፡

(ለ) በዚህ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 15 (9) የተመለከቱት መግለጫዎች በማሻሻያነት የቀረበውን ሃሣብ እና የማሻሻያውን አሳማኝ ምክንያቶች ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

(ሐ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች በማሻሻያ ሃሣቡ ላይ ምላሽ እና አስተያየት እንዲሰጡ ከሃያ አንድ (21) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡

(መ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል ከሚሉ ወገኖች አስተያየት ከተቀበለ በኋላ በተቀበለው አስተያየት ላይ ምላሹን ከሃያ አንድ (21) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በምላሹም፤

(1) ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ በመስጠት የመጨረሻ ውሳኔውን ያሰፍራል፤ወይም

(2) ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ ይሰጣል፣ አስፈላጊ ከሆነ በቀረበው ሃሣብ ላይ ማሻሻያ በማድረግ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች በመጀመሪያው ዙር በተቀመጠው ተመሳሳይ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደገና አስተያየት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡

(ሠ) ባለሥልጣኑ የመጨረሻ ውሳኔውን ከመስጠቱ በፊት በራሱ ሥልጣን ከሁለት ለበለጡ ዙሮች በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች ማሻሻያዎች ወይም አስተያየቶች እንዲያቀርቡ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

(ረ) በቀጥጥሩ ሂደት ባለሥልጣኑ በተቀበለው አስተያየት ላይ የሰጠውን ምላሽ እና የመጨረሻውን ውሳኔ በድኅረ ገጹ ማውጣት ይኖርበታል፡፡

(ሰ) በቁጥጥሩ ሂደት በጉዳዩ ያገባኛል በሚሉ ወገኖች ለባለሥልጣኑ የተሰጡ መረጃዎች ሚስጥራዊነትን በተመለከተ ባለሥልጣኑ የመረጃዎቹን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

9) የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ የቀረቡ የመሠረተ ልማት እና ኮሎኬሽን መጋራት አገልግሎቶች፣ የቴክኒክ ደረጃዎች እንዲሁም በመሠረተ ልማት እና ኮሎኬሽን ማጋራት አገልግሎቶች አቅራቢ የሚተገበሩ የደህንነት ደረጃዎች ዝርዝር የውል ቃሎችን እና ሁኔታዎችን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

10) የመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ የአገልግሎቱ የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች እንዴት እንደሚሻሻሉ የሚገልጽ ድንጋጌዎችን ማካተት አለበት፡፡

11) የመሠረተ ልማት ማጋራት ማጣቀሻ ሰነድ ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

(ሀ)የስምምነት ማዕቀፍ፤

(ለ) የሚቀርቡ የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች መግለጫ እና ተያያዥ የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች፤

(ሐ) በመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ የሚተገበሩ የደህንት ደረጃዎችን ጨምሮ በመሠረተ ልማት ማጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ በባለቤትነት ወደ ተያዙ ወይም በቁጥጥሩ ሥር ወደ አሉ ዝግጅቶች ወይም ቁሳዊ መሠረተ ልማት ለመግባት የሚያስችሉ ዝርዝር የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች፤

(መ) የአገልግሎት አሰጣጥን፣ዕቅድን እና ጥገናን ጨምሮ የአሠራር ሥርዐቶች፤

(ሠ) ክፍያዎች፣ የክፍያ መጠየቂያ ሥርዐቶች እና የውል ቃሎችና ሁኔታዎች ጨምሮ ንግድ ነክ ጉዳዮች፤

(ረ) የአገልግሎት አሰጣጥ ስምምነት፤

(ሰ) ለኮሎኬሽን ወይም ለመሠረተ ልማት መጋራት እንዲሁም ለተቀጥላ አገልግሎቶች ወይም ዝግጅቶች የቴክኒክ መስፈርቶችን ያለውን ቦታ ስፋትን ጨምሮ የአገልግሎቶች መጠንና አቅም መረጃዎች ልውውጥን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤ እና

(ሸ)የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂዎች የውል ቃሎችን እና ሁኔታዎችን ለማሻሻል የቀረቡ ሃሣቦችን እና ማሻሻያዎቹ የሚከናወንበትን የጊዜ ገደብ የሚያውቁበትን መንገድ ጨምሮ የማሻሻያ ሥርዐቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፡፡

## ክፍል ስድስት
## ኮሎኬሽን እና የመሠረተ ልማት መጋራት ክፍያዎች እና ወጪዎች

### 15.<u>የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች ክፍያዎች</u>

1) የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የመሠረተ ልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን ጠያቂዎችን በሚጎዳ ሁኔታ ለተዛማጅ ኩባንያዎች የተሻለ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ክፍያዎችን መስጠት አይችሉም፡፡

2) የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የመሠረተ ልማት አቅራቢ ለራሳቸው ከሚያቀርበው የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልገሎቶች የክፍያ ተመን ያነሰ ተጠቃሚ የማያደርግ ምክንያታዊ ክፍያዎች ማቅረብ አለባቸው፡፡

3) ለመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልገሎቶች የሚጠየቁ ክፍያዎች፤

(ሀ) በዚህመመሪያአንቀጽ 6 በተደነገገው መርሆዎች መሠረት የሚመሩ፤

(ለ)ጠያቂው ኦፕሬተር ለተጠየቁት አገልግሎቶች የግድ አስፈላጊ ላልሆኑ የሥራ መስኮች ክፍያ እንዳይፈጽም እያንዳንዱን አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ተነጣጥለው እንዲደራጁ የሚያደርግ፤ እና

(ሐ)በአዋጁ አንቀጽ 45 እና በባለስልጣኑ በፀደቀ ማናቸውም መመሪያ መሠረት ሕግን የተከተሉ፤

መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

4) የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልገሎቶች ክፍያዎች ተለይተው፤

(ሀ) የመሠረተ ልማት መጋራት ወይም የኮሎኬሽን አገልገሎቶች ዝግጅት ማቋቋሚያ እና መተግበሪያ ቋሚ የአንድ ጊዜ ክፍያዎች፤

(ለ) ጥቅም ላይ እየዋለ ላለ የኔትወርክ መሠረተ ልማት ወይም መገልገያዎች በየጊዜው የሚከፈሉ ክፍያዎች፤እና

(ሐ)ለተጨማሪ አገልግሎቶች የሚከፈሉ ተለዋዋጭ ክፍያዎች፤

ራሳቸውን ችለው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

5) ባለሥልጣኑ የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ ለመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አግልግሎቶች አግባብነት ባለው ገበያ ውስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዲኖረው የወሰነ እንደሆነ የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ የመሠረተልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን አገልግሎት የዋጋ ተመኖች እንዲፀድቅለት ከባለሥልጣኑ ዘንድ ፋይል ማድረግ አለበት፡፡

6) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ፋይል የተደረገን ማናቸውንም ታሪፍ እስከሚያፀድቅ ድረስ በአዋጁ አንቀጽ 45 (4) መሠረት ከትግበራ እንዲያዘገየው ለመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ መመሪያ ሊሰጥ ይችላል፡፡

7) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የመሠረተልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን አገልግሎት የዋጋ ተመንን እንዲያጸድቅ በቀረቡለት በሰላሣ (30) የሥራ ቀናት ውስጥ፤

(ሀ) ፋይል የተደረጉትን የዋጋ ተመንን በማጽደቅ፣ወይም

``` (ለ) ፋይል የተደረጉትን የዋጋ ተመንን ውድቅ በማድረግ፣ወይም

(ሐ) በአዋጁ አንቀጽ 46 እና በአዋጁ በአንቀጽ 35 እስከ 38 ወይም በባለስልጣኑ በፀደቀ ማናቸውም መመሪያ የተደነገጉትን ሥነ ሥርዐቶች መሠረት በማድረግ የዋጋ ተመኖቹን ለመገምገም እና ሕጋዊነታቸውን ለማረጋገጥ የቁጥጥር  ሂደት የማንቀሳቀስ ፍላጎት እንዳለው፤

በጽሑፍ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

8) ባለሥልጣኑ የዋጋ ተመኖቹ እንዲፀድቁ ለቀረበው ጥያቄ በሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ ተመኖቹ እንደፀደቁ ይቆጠራሉ፡፡

9) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 እስከ 6 የተደነገጉት ቢኖሩም፣ ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 46፣ በዚህ መመሪያ ወይም በባለስልጣኑ በፀደቀ ማናቸውም መመሪያ መሠረት በራሱ ሥልጣን በማናቸውም ጊዜ የመሠረተልማት መጋራት  እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች ማናቸውም ተመንን ለመገምገም እና ሕጋዊነቱን ለማረጋገጥ የቁጥጥር ሂደቱን ማንቀሳቀስ ይችላል፡፡

10) በአዋጁ አንቀጽ 45 መሠረት ባለሥልጣኑ የታሪፎችን ሕጋዊነት እና የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች ክፍያዎችን ለመወሰን ደረጃዎችንና ሥነ ሥርዐቶችን የሚደነግጉ መመሪያዎችን ማውጣት ይችላል፡፡

## 16. <u>የሂሳብ ደብተር መለያየት</u>

1) ባለሥልጣኑ የመሠረተልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን አቅራቢ ለመሠረተልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን አግልግሎቶች አግባብነት ባለው ገበያ ውስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የወሰነ እንደሆነ እና የመሠረተልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን አቅራቢ በተጨማሪ የችርቻሮ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን በችርቻሮ የሚሰጥ ከሆነ፣የአገልግሎቶቹ አካል የሆኑትን ወጪዎችና ገቢዎች   ሁሉ ለመለየት የመሠረተልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን አቅራቢ የመሠረተልማት ማጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶቹ በሕግ መሠረት ራሱን ችሎ እንደሚያከናወን ኩባንያ የተለዩ የሂሣብ መዝገቦችን መያዝ ይኖርበታል፡፡

2) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የሂሳብ መለያየት እንዴት እንደሚወሰን የሚገልጹ መመሪያዎች በራሱ ሥልጣን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት
## ስለምደባ፣ አቅም ይዞ ስለማቆየት እና ለአገልግሎት ዝግጁ ስለማድረግ

## 17.<u>አቅምን ስለመመድብ እና ይዞ ስለማቆየት</u>

1) ለመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አግልግሎቶች የሚቀርቡ ጥያቄዎች በመሠረተልማት ማጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ የሚስተናገዱትና አገልግሎቱም የሚሰጠው ቀደሞ የመጣ በቅድሚያ ያገኛል የሚለውን መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡
```

2) የራሱን አዲስ የኔትወርክ መሠረተ ልማትን ወይም መገልገያዎችን የሚዘረጋ ወይም የሚገነባ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር በዚህ መመሪያ አባሪ ለ በተጠቀሱት ሳይወሰን ከመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂዎች ጋር ለመጋራት ካለው አጠቃላይ ቦታ ወይም አቅም ቢያንስ ሃምሣ በመቶውን (50%) ይዞ ማቆየት አለበት፡፡ በባለሥልጣኑ በተለየ ሁኔታ መመሪያ ካልተሰጠበት በስተቀር፣ ለማጋራት ታስቦ ተይዞ እንዲቆይ የተደረገው አቅም ወይም ቦታ ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ይመደባል፤

(ሀ) ለመጀመሪያው የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ ለመጋራት ተይዞ እንዲቆይ ከተደረገው አቅም ወይም ቦታ ውስጥ ከሃምሳ በመቶ (50%) ያልበለጠ ይመደብለታል፡፡

(ለ) ቀጥሎ የሚመጡ ሁሉም የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂዎች ከተረፈው የተወሰነውን ወይም ሁሉንም ለጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

3) አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች አዲስ የኔትወርክ መሠረተልማት በመዘርጋት ወይም በመገንባት ከመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ ጋር ቅንጅት ከፈጠሩ በባለሥልጣኑ በተለየ ሁኔታ መመሪያ ካልተሰጠበት በስተቀር፣ የተሳተፉት ኦፕሬተሮች በቡድኑ ውስጥ ካሉት ተሳታፊ ኦፕሬተሮች ውጭ ካሉ የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂዎች ጋር ለመጋራት ካሉት የጋራ አጠቃላይ ቦታ ወይም አቅም ቢያንስ ሃያ በመቶውን (20%) ይዘው ማቆየት አለባቸው፡፡

4) የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ ከመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂዎች ጋር የሚጋራው አቅም ወይም ቦታ ለመሠረተልማት መጋራት እና ለኮሎኬሽን ጠያቂዎች ያልተመደበ፣ ተመድቦም ከሆነ ከተመደበ ወይም ተይዞ እንዲቆይ ከተደረገ ከሦስት (3) ዓመት ያላነሰ ከሆነ ፣ በባለሥልጣኑ በተለየ ሁኔታ መመሪያ ካልተሰጠበት በስተቀር፣ የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ ይህንኑ ተራፊ አቅም ወይም ቦታ ለራሱ ወይም ለማንኛውም የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ የሥራ መስኩን ወይም አቅሙን ወይም ሁለቱንም እንደገና ሊመድበው ይችላል፡፡

18.<u>ለአዲስ መሠረተልማት ተደራሽነትን የማስጠበቅ ግዴታ</u>

1) አዲስ የኔትወርክ መሰረተልማት ወይም መገልገያዎችን ለመገንባት ሲታቀድ እና ሲገነባ፣ሁሉም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች አሁን ያለውን የኮሎኬሽን እና የመሠረተልማት መጋራት ፍላጎት ወይም አዲሱን የኔትወርክ መሰረተልማት ወይም መገልገያዎች ማስፋፊያን ወይም ግንባታን ተከትሎ ወደፊት የሚኖረውን የኮሎኬሽን እና የመሠረተ ልማት ማጋሪያ ፍላጎትን በተገቢው መጠን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ አዲሱ መሠረተ ልማት የሚታቀደው እና የሚገነባው ከመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂዎች ጋር የሚደረገውን የኮሎኬሽን እና የመሠረተልማት መጋራትንበዚህ መመሪያ መሰረት ለማሳለጥ ነው፡፡

2) አዲስ የኔትወርክ መሠረተልማት እና መገልገያዎችን ለመዘርጋት ወይም ለመገንባት የሚያቅድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለወደፊቱ እነዚህን የኔትወርክ መሠረተ ልማት እና መገልገያዎችን በምክንያታዊነት ተደራሽ እንዲያደርጉ የልማት ዕቅዱን ለቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ማጋራት አለበት፡፡

3) በአሁኑ ወቅት ወይም ወደፊት ይኖራሉ ተብሎ ከሚገመቱት ደንበኞችን የማገልገል ፍላጎቶች ጋር የማይዛመዱ ገመዶችን፣መሳሪያዎችን ወይም ሌሎች መገልገያዎችን የሚዘረጋ እና ተገቢ ባልሆነ ቦታ አጠቃቀም ምክንያት የኮሎኬሽን እና መሠረተልማትን አሁን ካሉት እና አቅም ካላቸው የመሠረተልማት መጋራት ጠያቂዎች ጋር መጋራትን የሚከለክል ወይም የሚገድብ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር መኖር የለበትም

4) የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነትን የሚመለከቱ የኔትወርክ መሠረተ ልማት ክፍሎችን ወይም መገልገያዎችን ለማሻሻል፣ ለማስፋፋት ወይም ቦታ ለመቀየር ያቀደ እንደሆነ የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ የታሰበውን ለውጥ በመግለጽ ለመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ የቀረበን የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች መስተጓጎልን ለመቀነስ ከታቀደ ዕቅድ ጋር ከአንድ መቶ ሃያ (120) የሥራ ቀናት ያላነሰ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ለስምምነቱ ተዋዋይ ወገኖች መስጠት ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ስምንት
## ግዴታን ስለማላላት

19.<u>ግዴታ እንዲላላ ስለመጠየቅ</u>

1) በዚህ መመሪያ የተገለጸ ማናቸውም ድንጋጌ ቢኖርም፣የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ በዚህ መመሪያ የተጣለበትን የተወሰነ ግዴታ እዲላላለት ባለሥልጣኑን መጠየቅ የሚችለው፤

   (ሀ) ባለሥልጣኑ የመሠረተልማት መጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን አቅራቢን በመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች አግባብ ባለው ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዲኖረው ያልወሰነ እንደሆነ፤

   (ለ) ምንም እንኳን ባለሥልጣኑ አግባብ ባለው የመሠረተልማት መጋራት እና/ወይም የኮሎኬሽን አገልግሎቶች ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዲኖረው የወሰነ ቢሆንም አግባብ ባለው ገበያ የነበረው ውድድር በመለወጡ የመሠረተልማት መጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን አቅራቢው ቀደም ሲል የነበረውን የገበያ ድርሻ ያጣ እንደሆነ፤ ወይም

   (ሐ) ምንም እንኳን ባለሥልጣኑ አግባብ ባለው የመሠረተልማት መጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን አገልግሎቶች ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የወሰነ ቢሆንም በተወሰነ መልክዓ ምድር አካባቢ በተወሰኑ ሁኔታዎች የሚደረገው ውድድር በመልክዓ ምድሩ አካባቢ የግዴታዎች መላላትን የሚጠይቅ የሆነ እንደሆነ፤

   (መ) በአንድ የተወሰነ የኔትወርክ መሰረተልማት ክፍል ወይም አገልግሎት ወስጥ ያሉ ሁኔታዎች በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ግዴታዎችን አሟልተው ወደ ተግባር ለመለወጥ ወይም አዋጪ ለማድረግ ያላስቻለ እንደሆነ ነው፡፡

2) ግዴታዎች እንዲላሉለት ለባለሥልጣኑ ጥያቄ የሚያቀርብ የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ የትኛው ግዴታ እና ከመመሪያው የትኛው አንቀጽ እንዲላላለት በመወሰን በጽሑፍ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

3) ባለሥልጣኑ ግዴታዎች እንዲላሉ በጽሑፍ ለቀረበው ጥያቄ በሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ፤

   ((ሀ) ከተገቢው ማብራሪያ ጋር ጥያቄው ውድቅ መሆኑን፤

   (ለ) ጥያቄውን ለመገምገም ተጨማሪ መረጃ የሚፈልግ መሆኑን፤ ወይም

   (ሐ) በአዋጁ ከአንቀጽ 35 እስከ አንቀጽ 38 በተደነገጉት ሥነ ሥርዐቶች መሠረት ጣልቃ በመግባት አስገዳጅ ውሳኔ ለመስጠት የወሰነ መሆኑን፤

   በመግለጽ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

3) ባለሥልጣኑ ለአንድ መሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ በዚህ መመሪያ የተመለከተው የተወሰነ ግዴታ እንዲላላለት ሲወስን የህ የግዴታ መላላት የሚቆየው ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሲሆን ጊዜው ካበቃ በኋላም የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ ግዴታው እንዲላላለት እንደገና መጠየቅ ይችላል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ
## ስለኮሎኬሽን

### 20.ኮሎኬሽን የኢንተርኮኔክሽን አካል ስለመሆኑ

1) ኮሎኬሽን ለኢንተርኮኔክሽን የሚደረገው ድርድር አካል ሆኖ በቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ኢንተርኮኔክሽን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚገዛ ይሆናል፡፡

2) እያንዳንዱ ዋና ኦፕሬተር በተለይም ባለሥልጣኑ በሚወስነው መሰረት ተፅእኖ ፈጣሪ ኦፕሬተሮች የተለያዩ የኮሎኬሽን ክፍሎች ዋጋ ዝርዝሮችን ጨምሮ አገልግሎቶቹ ለሽያጭ መቅረባቸውን በመሠረተ ልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነዶቻቸው ውስጥ ማካተት አለባቸው፡፡

3) ከሌላ ኦፕሬተር ጋር ግንኙነት መፍጠር የሚፈልግ ኦፕሬተር ለሥራው ተስማሚ የሆነውን የኮሎኬሽን ዓይነት የመምረጥ ነፃነት አለው፡፡

4) ለቁሳዊ ኮሎኬሽን ጥያቄ የቀረበ እንደሆነና ኮሎኬሽኑ አዋጪ አለመሆኑ ከተረጋገጠ የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎት አቅራቢ ኮሎኬሽንን በምናባዊ መንገድያቀርባል፡፡

5) ምናባዊ ኮሎኬሽን አዋጪ ሆኖ ካልተገኘ በርቀት በሚደረግ ግንኙነት መተካት ይኖርበታል፡፡

6) በርቀት በሚደረግ ግንኙነት የሚቀርብ የኮሎኬሽን ጥያቄ የተሟላ አቅም አለመኖርን፣ የደህንነት ምክንያቶችን፣ አስተማማኝነትን ወይም ሌላ አጠቃላይ የምህንድስና ምክያቶችን ጨምሮ በማናቸውም ምክንያት ውድቅ ሊሆን አይችልም፡፡

7) በግልጽ ተፈጻሚ እንዳይሆን ካልተደረገ በስተቀር፣ የኮሎኬሽን የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች በአጠቃላይ ለመሠረተ ልማት መጋራት ላይ ተፈጻሚ በሚሆኑት ደንቦች ይገዛል፡፡

## ክፍል አሥር
## ስለሕትመት

### 21. በባለሥልጣኑ የሚታተም የመሠረተልማት መረጃ

1) ባለሥልጣኑ ለመሠረተ ልማት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ አግባብ ባላቸው ገበያዎች ጉልህ የገበያ ድርሻ ባለው በመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ ባለቤትነት ወይም ቁጥጥር ሥር ያለ የኔትወርክ መሠረተ ልማት እና አገልግሎቶችን የሚመለከቱ የኔትወርክ መሠረተልማት እና መገልገያዎች የተሟላ እና ወቅታዊ መረጃ በየጊዜው ያሳትማል ወይም መታተማቸውን ያረጋግጣል፡፡

2) ባለሥልጣኑ ለመሠረተ ልማት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች አንድን የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ አግባብ ባላቸው ገበያዎች ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዲኖረው ከወሰነ የመሠረተ ልማት መጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን አቅራቢ ስለአገልግሎቶቹ እና ስለመሠረተ ልማቱ፤

   (ሀ) ከመሠረተልማት መጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን ጠያቂዎች እየተጋራ ያለውን፤ወይም፣

   (ለ) ለመጋራት ዝግጁ የሆኑትን፤

(ሐ) ለመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂዎች ጋር ተጋርቶት ያለውን ክፍት ቦታ ወይም አቅም እና ለመጋራት ዝግጁ የሆኑትን፤ ተይዘው ያሉትን ክፍት የሥራ መስኮችን፤ አቅምን ጨምሮ እና በእነዚህም ሳይወሰን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተውን መረጃ፤

በተመለከተ ለባለሥልጣኑ መረጃ መስጠት አለበት።

3) ከባለሥልጣኑ የቀረበውን የጽሑፍ ጥያቄ ተከትሎ የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተውን መረጃ ጥያቄው በቀረበ በሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል።

4) ባለሥልጣኑ ለሌሎች የተጋሩ ወይም ለመጋራትዝግጁ  የሆኑ የመሠረተ ልማት አገልግሎቶችን በተመለከተ ከመሠረተ ልማት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ የተቀበለውን መረጃ በራሱ ጊዜ በድኅረ ገጹ ሊያወጣው ይችላል።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) የተደነገጉት ቢኖሩም፣ ሁሉም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች በሚቀርብላቸው ጥያቄ መሠረት በባለቤትነት የያዙትን ወይም በቁጥጥራቸው ሥር ያሉትን የሁሉንም ማማዎች እና ረዣዥም ቋሚዎችን ዝርዝር ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለባቸው። ዝርዝሩም ስለእያዳንዱ ረዣዥም ቋሚ እና ማማ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፤

(ሀ) የማማውን  ቦታ ስለሚያመላክት የጂፒኤስ መጋጠሚያዎች፣

(ለ) መከላከያ አጥር ፣ብቸኛ ምሰሶ(ሞኖፖል)፣ጊድ ወዘተ ጨምሮ ስለማማው መዋቅር ዓይነት፣

(ሐ)ማማው ስለተሠራበት መሣሪያ፤

(መ)ከመሬት በላይ ስላለው ከፍታ፤

(ሠ)ስለከፍተኛው የክብደት መጠን፤

(ረ)የቦታውን ስፋት በካሬ ጫማ እና ሌሎች ባህርያትን ጨምሮ ስለሥራ ቦታው ዝርዝር/አቀማመጥ/፤

(ሰ) ከኃይል ማከፋፈያ፣ከጀነሬተሮች፣ወዘተ የተያያዘ መረጃን ጨምሮ ስለኃይል ማግኛ።

6) አንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ማናኛውም አይነት አዲስ የማማ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ሊገነባ ከታሰበው ማማ ወይም ማማዎች ጋር በተያያዘ በዘህ አንቀጽ ንዑስ (5) የተገለጹ መረጃዎችን ስለትክክለኛነታቸው ማረጋገጫ በመስጠት በሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።

7) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) መሠረት ከቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የተቀበለውን መረጃ የሚይዝበት የመረጃ ቋት ያደራጃል ፣ያስተዳድራል፣በጽሑፍ ጥያቄ ሲቀርብለት የዚህኑ መረጃ ኮፒ ለቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር በአሥራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ውስጥ መስጠት ይኖርበታል።

8) ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) መሠረት ከቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የተቀበለውን ከማማዎቹ እና ከረዣዥም ቋሚዎች ጋር የተያያዘ መረጃ በራሱ ድረ ገጽ ላይ ሊያወጣው ይችላል።

## ክፍል አሥራ አንድ
## አለመግባባትን ስለመፍታት

### 22.<u>የኮሎኬሽን እና የመሠረተ ልማት መጋራት አለመግባባትን ስለመፍታት</u>

1) የመሠረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች ጥያቄ ምክንያታዊነትን በተመለከተ ወይም ተዋዋይ ወገኖቹ ስምምነት ላይ ባለመድረሳቸው ወይም የመሠረተልማት መጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን ስምምነት ባለመፈጸሙ የሚነሳ ማናቸውም አለመግባባት መፍትሔ እንዲያገኝ ከተዋዋይ ወገኖቹ በአንዱ ለባለሥልጣኑ ሊቀርብ ይችላል፡፡

2) አለመግባባቶች በባለሥልጣኑ እንዲፈቱ የሚጠይቅ ማንኛውም ወገን ተዋዋይ ወገኖቹ ስምምነት ላይ መድረስ ካቃተባቸው ቀን በኋላ በስልሳ (60) የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡

4) ባለሥልጣኑ ጣልቃ እንዲገባ የቀረበውን ጥያቄ ተከትሎ ጥየቄውን በተቀበለ ሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ፤

   ( ሀ) ጣልቃ ለመግባት ወይም ላለመግባት ከመወሰኑ በፊት ከተዋዋይ ወገኖቹ ተጨማሪ መረጃዎችን በመጠየቅ፤

   (ለ) ጣልቃ ላለመግባት ከወሰነ ላለመግባት የወሰነበትን ከእነ አሳማኝ ምክንያቱ በጽሑፍ በማስፈር፤ ወይም

   (ሐ) በባለሥልጣኑ የክርክር መፍቻ መመሪያ በተደነገጉት ሥነ ሥርዐቶች መሠረት ጣልቃ ለመግባት መወሰኑን፤

   ለጠያቂው ወገን ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አሥራ ሁለት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 23. <u>ማሻሻያ</u>

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በማናቸውም ጊዜ ከአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ይህንን መመሪያ ማሻሻል ይችላል፡፡

### 24.<u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከ ___ ቀን 2012 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ______ ቀን ______________ 2012 ዓ.ም.

**ኢንጂነር ባልቻ ሪባ**

**የኢትዮጵያ ኮሙኒከሽን ባለሥልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**

## አባሪ ሀ

## የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልገሎቶች መግለጫ

ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት የአገልግሎቶች ክፍሎች/መደቦች/ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆንበትን የወል የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልገሎቶች ዓይነት የሚያብራራ ነው፡፡ የተወሰኑት አገልግሎቶች ለመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ በንብረቱ ባለቤት የሚሰጥ የመጠቀም መብትን ሊጨምር ይችላል፡፡

1) **ኮሎኬሽን፡-** የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ በራሱ ኔትወርክ መሠረተ ልማት በቦታው፣ በአገልግሎቶቹ ወይም በቅጥር ግቢው ለመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ የሚያቀርበው አገልግሎት ነው፡፡ የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ የራሱን የቴሌኮሙኒኬሽን ማስተላለፊያ መሣሪያዎችን ለመትከል ለመጠገን እና ለማካሄድ በሳምንት 24 ሰዓት ወይም 7 ቀናት ወደ ኮሎኬሽን ቦታ ወይም ክፍል መግባት ይችላል፡፡ የኮሎኬሽን አገልግሎት በተለያዩ ዘዴዎች ሊሰጥ ይችላል፡፡

ሀ) የተመደበ ኮሎኬሽን፡- የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎቹን እንዲዘረጋ ፍላጎቱን መሠረት አድርጎ የሚመድበው፣ ለይቶ የሚያዘጋጀው እና ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ነው፡፡

ለ) ተጎራባች ኮሎኬሽን፡-የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ ካለው አገልግሎት ተጎራባች በሆነ ራሱን በቻለ ቦታ ሆኖ ተነጥሎ ባለ ተቋም ውስጥ ለመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ የሚያቀርበው ነው፡፡

ሐ) ርቀት ያለው ኮሎኬሽን፡- የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ ለመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ በታጠረ ወይም በተከለለ ሥፍራ ቦታ የሚያቀርብበት ሆኖ ቦታውም ካሉት የአገልግሎት መሣሪያዎች የራቀ አካባቢ ነው፡፡

መ) ማጣመር፡-የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ ለመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ በወለል ላይ ባለ ቦታ ወይም መደርደሪያ መሣሪያውን ጎን ለጎን እንዲያስቀምጥ የሚያቀርበው ነው፡፡

ሠ) ቨርቹዋል ኮሎኬሽን፡-የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ ከኮሎኬሽን ቦታ ጋር ቁሳዊ ተደራሽነት ሳይኖር ከመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ አገልግሎቶች ጋር ግንኙነት እንዲፈጠር የሚያደርግበት ነው፡፡ የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ የራሱን የማስተላለፊያ መሣሪያ ሊያቀርብ ወይም ከመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ ሊከራይ ይችላል፡፡ መሣሪያዎችን የሚዘረጋው፣ የሚያንቀሳቅሰው እና የሚጠግነው የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ ነው፡፡ የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ ለምናባዊ ኮሎኬሽን ቦታ ወይም መሣሪያ ተደራሽነት ወይም ግንኙነት አይኖረውም፡፡ ሆኖም በኤሌክትሮኒክ መንገድ የኮሙኒኬሽን መሣሪያውን ሊቆጣጠር ይችላል፡፡

2) ለማስተላፊያ ቱቦ የሚኖር ተደራሽነት፡- መሬት ለመሬት የሚሄዱ ሽቦዎች ለተሸፈኑበት ወይም ለሚያልፉበት  ኮንድዩቶች ወይም ቧንቧዎች ተደራሽ የሚያደርግ ነው፡፡ የማስተላለፊያ ቱቦዎቹ ሽቦዎቹን የሚከላከሉ እና ተጨማሪ ቁፋሮ ሳያስፈልግ ተጨማሪ ሽቦዎችን ለማስገባት ወይም ያለውን ለማውጣት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ለማስተላለፊያ ቱቦዎች የሚኖር ተደራሽነት የጥገና ማከናወኛ ትናንሽ ጉድጓዶችን/ማንሆሎች/ እና የእጅ ማስገቢያ ቱቦዎች/ ሃንድሆሎች/  ወይም ሕንፃዎች የመሳሰሉ ተዛማጅ ግንባታዎችን እንዲሁም ለኃይል እና ለአየር ማቀዝቀዣ አገልግሎቶች ተደፈራሽ የሚያደርጉትን ሊያካትት ይችላል፡፡

3) ለማማዎች እና ለረዣዠም ቋሚዎች የሚኖር ተደራሽነት፡-የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ የራሱን የማስተላለፊያ መሣሪያ እና ሽቦዎች ለመዘርጋት ዓላማ በመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽንአቅራቢ ባለባቤትነት እና ቁጥጥር ሥር ያለን ማማን እና ረዣዠም ቋሚን እንዲጠቀም የሚፈቅድበት አገልግሎት ነው፡፡ አገልግሎቱም ሕንፃዎችን፣ የሥራ ቦታዎችን፣ ኃይልን እና አየር ማቀዝቀዣን ለመሳሰሉ ተዛማጅ ግንባታዎች ተደፈራሽ የሚያደርጉትን ያካትታል፡፡

4) ጥቁር ፋይበር፡-የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ ለመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ የሚያከራየው ነጠላ ፋይበር ወይም የብዙ ፋይበሮች ስብሰብ ነው፡፡ ሆኖም የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ የማስተላለፊያ መሣሪያውን ከተከራየው ፋይበር ጋር ማያያዝ አይችልም፡፡ አገልግሎቱም የጥገና ማከናወኛ ትናንሽ ጉድጓዶችን እና የእጅ ማስገቢያ ቱቦዎችን፣ ሕንፃዎችን፣ የሥራ ቦታዎችን፣ ኃይልን ወይም የሥራ እና አየር ማቀዝቀዣን ለመሳሰሉ ተዛማጅ ግንባታዎች ተደፈራሽ የሚያደርጉትን ያካትታል፡፡

5) አንበንድልድ ሎካል ሉፕ፡- የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ ኮፐር ፔሮችን ከመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አቅራቢ በኪራይ የሚያገኝበት ነው፡፡ የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ የድምፅ እና የዳታ አገልግሎቶች ለመቆጣጠር የሚያስችለውን ከዋናው ማከፋፈያ ፍሬም እስከ ደንበኛ ያሉትን የኮፐር ፔሮችን ይቆጣጠራል፡፡

6) ለኢንተርኮኔክሽን መዳረሻ ነጥቦች፡- እነዚህ ነጥቦች ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ወደ ተገናኙበት አገልገሎቶች፣ የሥራ ቦታዎች ወይም ሕንፃዎች ተደራሽ የሚያደርግ ነው፡፡ አገልግሎቱ ማያያዣዎችን፣ ኃይልን እና የአየር ማቀዝቀዣን ሊያካትት ይችላል፡፡

## አባሪ ለ

## ለመሠረተ ልማት መጋራት ሊውሉ የሚችሉ የመሠረተልማት አይነቶች

**1) ቋሚ መሠረተልማት (Passive Infrastructure)**

a. Rights-of-way
b. Antenna mast and tower structures
c. Dark fiber
d. Poles
e. Ducts
f. Trenches
g. Space in buildings
h. Shelters
i. Air conditioning
j. Sub-Loop (Wire or Cable)
k. Local Loop (Wire or Cable)
l. Electric power (public or private source)
m. Grounding/Earthing
n. In-House wiring.

**2) ገባሪ መሠረተልማት (Active Infrastructure)**

a. Radio Access Network (RAN) (MORAN or MOCN)
    i. BTS/Node
    ii. B/e-Node
    iii. antennae
    iv. feeder cable
    v. RAN
    vi. microwave radio equipment
    vii. BSC/RNC

b. In-Building Solutions (IBS)
    viii. Distributed Antenna System (DAS),
    ix. antennae,
    x. feeder cable,
    xi. splitters, and
    xii. Combiners.

c. Optical/Wired Transmission Links.
d. Multiplexer (MUX)
e. Synchronous Digital Hierarchy (SDH)
f. Dense Wavelength Division Multiplexer (DWDM)